Seattle Office of Labor Standards

# Paid Sick እና Safe Time እና COVID-19 -- በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎችና መልሶች

**የተሻሻለበት ቀን 4-8-2020**

ሰራተኞች Paid Sick እና Safe Time (PSST) መጠቀማቸውን በማረጋገጥ አሰሪዎችና ሰራተኞች የማህበረሰቡን ደህንነትና ጤንነት ለማስጠበቅ የድርሻቸውን መወጣት ይችላሉ! ይህ ሰነድ የ Seattle Paid Sick እና Safe Time ሕግን በተመለከተ እርስዎ ለሚኖሩዎት ጥያቄዎች መልሶችን ይሰጣል። ተጨማሪ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት እባክዎ የ Office of Labor Standardsድረ ገጽን ይጎብኙ።

የ Paid Sick እና Safe Time መመሪያ:-

- ሰራተኞችና ልጆች በሚታመሙበት ወቅት ቤት ውስጥ መቆየታቸውን፣ ከሌሎች ሰራተኞች፣ ከትምህርት ቤትና ከደንበኞች መራቃቸውን በማረጋገጥ የማህበረሰብ ጤናን ያስጠብቃል
- የበሽታን ስርጭት በመገደብ ይበልጥ ምርታማ የሆኑ የስራ ቦታዎችን ይፈጥራል
- ሰራተኞች ደመወዛቸውን ሳያጡ ጤንነታቸውን መንከባከብ ስለሚችሉ፣ ኢኮኖሚያዊ ደህንነትን ይገነባል

በዚህ ጥያቄ እና መልስ ውስጥ ያልተሸፈነ ጥያቄ አለዎት? የ Paid Sick and Safe Time ድረ ገጻችንንይጎብኙ፣ በስልክ ቁጥር 206-256-5297 ይደውሉ ወይም በኤሌክትሮኒክ መንገድ ያግኙን፡

- ጥያቄዎችና ቅሬታዎች ያላቸው ሰራተኞች  አንላይን ጥያቄ ያቅርቡ ወይም በቀጣዩ አድራሻ ኢሜይል ያድርጉ:- workers.laborstandards@seattle.gov።
- የቴክኒክ እገዛ የሚፈልጉ አሰሪዎች  አንላይን ጥያቄ ያቅርቡ ወይም በቀጣዩ አድራሻ ኢሜይል ያድርጉ:- business.laborstandards@seattle.gov።

---

**አዲስ እና አስፈላጊ!** **በኤፕሪል 8፣ 2020፣** Office of Labor Standards **ጊዜያዊ፣ የድንገተኛ ጊዜ ደንብ** ያወጣ ሲሆን ይህም አንድ ሰራተኛ በ COVID-19 ወረርሺኝ ወቅት መጠየቅ የሚችልበትን የማረጋገጫ ዓይነቶችን የሚቀይር ነው። ከአሁን ጀምሮ እስከ ጁን 7፣ 2020 ድረስ፣ አንድ ሰራተኛ ለ PSST ጥቅም ማረጋገጫ የጤና እንክብካቤ አቅራቢ ሰነዶችን መጠየቅ አይችልም። በምትኩ፣ አንድ ሰራተኛ ማረጋገጫ መጠየቅ ከመረጠ፣ ሰራተኛው አማራጭ የማረጋገጫ መንገዶችን መለየትና መስጠት አለበት። ማስታወሻ:- ሰራተኞች ለሶስት እና ከዚያ በታች ቀኖች የቀሪ ማረጋገጫ መጠየቅ አይችሉም። ስለ ጊዜ፣ የሚፈቀዱ ማረጋገጫ፣ እና ስለዚህ አዲስ ደንብ የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ የኛን ድረ ገጽ ወይም አጠቃላይ የሚጠየቁ ጥያቄና መልሶች ይመልከቱ።

**አዲስ ነገር!**  ይህ ሕግ የተሻሻለው ማርች 16/2020 ነው። እነዚያ ለውጦች ተግባራዊ የተደረጉት ከማርች 18/2020 ጀምሮ ነው። ይህ ሰነድም እነዚያን ለውጦች ለማንጸባረቅ ሲባል እንዲሻሻል ተደርጓል።

## Paid Sick እና Safe Time (PSST) ምንድን ነው?

Paid Sick እና Safe time አሰሪው ለሰራተኞች ከክፍያ ጋር የሚሰጠው የእረፍት ጊዜ ሲሆን፣ ሰራተኞችም ይህን እረፍት ለሚከተሉት ጉዳዮች መጠቀም ይችላሉ:-

- ራሳቸው ወይም የቤተሰባቸው አባል ሲታመም፣ ሲጎዳ ወይም የጤና ችግር ሲያጋጥማቸው ለመንከባከብ
- ለራሳቸው ወይም ለቤተሰባቸው አባል የሕክምና ወይም የቅድመ መከላከያ እንክብካቤ ለማግኘት ወደ ሐኪም ለመሄድ
- ሰራተኞች ራሳቸውን ለይተው እንዲያስቀምጡ በሕዝብ ጤና ባለስልጣናት ምክረ ሃሳብ ከተሰጣቸው
- የቤተሰባቸው አባል ት/ቤት ወይም የመንከባከቢያ ቦታ ሲዘጋ
- የስራ ቦታቸው በጤና ጉዳዮች ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ሲዘጋ
- 250 ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞችን በመላው ዓለም ለሚያስተዳድር የንግድ ስራ፡ የስራ ቦታቸው በማንኛውም የጤና ወይም የደህንነት ምክንያት ሲዘጋ

## PSST የሚያገኙ ሰራተኞች የትኞቹ ናቸው?

Seattle ውስጥ፣ አሰሪዎች ለሁሉም ሰራተኞች paid sick እና safe time እንዲሰጡ ሕጉ ያስገድዳል። በዚህም ውስጥ የሚካተቱት የሙሉ ጊዜ፣ የትርፍ ጊዜ፣ የሚታለፉና የማይታለፉ ሰራተኞች ናቸው።

## ሰራተኞች ምን ያህል PSST ያገኛሉ?

Paid Sick እና Safe Time በጊዜ ሂደት የሚገኝ ነው። መጠኑ የሚመሰረተውም አንድ ሰራተኛ በሰራበት የስራ ሰዓትና በአሰሪያቸው የንግድ ስራ ዓይነት ላይ ነው።  ለዝርዝር መረጃ፣ የ Office of Labor Standards ድረ ገጽ ይጎብኙ።

## አንድ ሰራተኛ በአንድ ጊዜ መውሰድ የሚችለው ምን ያህል PSST ነው?

አንድ ሰራተኛ በጊዜ ሂደት የተጠራቀመለትንና የተጨመረለትን ሰዓት መጠን በተቻለ መጠን ዝቅተኛውን መጠቀም ያለበት ሲሆን፣ ይህም አሰሪው የስራ ሰዓትን ለመከታተል እንዲያመቸው ነው (ከአንድ ሰዓት ግን መብለጥ የለበትም)።

## አንድ ሰራተኛ የ PSST ቀሪ ሂሳቡን እንዴት ማግኘት ይችላል?

በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ ሕጋዊ ምክር ባለመሆኑ ሕጎችና ደንቦችን በመተካት አገልግሎት መስጠት የለበትም።
የተሻሻለበት ቀን:- 4/8/2020

አሰሪዎች ደመዎዝ በከፈሉ ቁጥር ይህን መረጃ ማጋራት አለባቸው። በርካታ አሰሪዎች ይህን መረጃ የክፍያ ቁራጩ ላይ ይጽፉታል ወይም በኦንላይን የፔይሮል መረጃ ስርዓት ላይ እንዲታይ ያደርጉታል።

**አንድ ሰራተኛ <u>የስራ ቦታው፣</u> እንደ COVID-19 ባለ የጤና ችግር ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ቢዘጋ፣ PSST መጠቀም ይችላል?**
አዎ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሰረት፦

- የሰራተኞች የስራ ቦታ ከጤና ጋር በተያያዘ ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ሲዘጋ ሁሉም አሰሪዎች ሰራተኞች PSST እንዲወስዱ መፍቀድ አለባቸው።
- 250 ወይም ከዚያ በላይ የሚሆኑ የሙሉ ጊዜ ሰራተኞችን በመላው ዓለም የሚያስተዳድሩ አሰሪዎች፣ የስራ ቦታቸው የስራ እንቅስቃሴ በማንኛውም የጤና ወይም የደህንነት ምክንያት ከቀነሰ ወይም ከተዘጋ፣ ሰራተኞች PSST እንዲወስዱ መፍቀድ አለባቸው። የመዝጋት ውሳኔው በመንግስት ባለስልጣን መታዘዝ ወይም መመከር የለበትም።

**የመንግስት ባለስልጣን ማነው?**
የመንግስት ባለስልጣን ማለት የመንግስት ሰራተኛ ሆኖ የስራ ቦታ ወይም ትምህርት ቤትን የመዝጋት ስልጣን የተሰጠው ነው። በዚህም ውስጥ፣ የአካባቢ፣ የግዛት ወይም የፌዴራል ባለስልጣናትና የማህበረሰብ ጤና ሃላፊዎች (ለምሳሌ፡ Seattle - King County Public Health፣ Center for Disease Control (የበሽታ ቁጥጥር ማዕከል)፣ ወይም the State Department of Health (የጤና የግዛት ክፍል)) ወይም የሕዝብ ትምህርት ቤት ዋና ተቆጣጣሪ ወይም ርዕሰ መምህር ይካተታሉ።

***ሰራተኞች የቤተሰባቸው አባል ት/ቤት ወይም የመንከባከቢያ ቦታ ሲዘጋ በ PSST መጠቀም ይችላሉ?***
አዎ። አንድ ሰራተኛ የቤተሰባቸው አባል ት/ቤት ወይም የመንከባከቢያ ቦታ ሲዘጋ በ PSST መጠቀም ይችላሉ። ከማርች 2020 ማሻሻያዎች በፊት፣ *የልጃቸው* የመንከባከቢያ ቦታ ወይም ት/ቤት ከጤና ጋር በተያያዘ ምክንያት በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ ከተዘጋ፣ ሰራተኞች PSST መጠቀም ይችሉ ነበር። አንድ ሰራተኛ የትኛውም *የቤተሰቡ አባል* የመንከባከቢያ ቦታ ሲዘጋ በ PSST መጠቀም ይችላል። በተጨማሪም፣ የመዝጋት ምክንያቱ ከጤና ጋር በተያያዘ ወይም በመንግስት ባለስልጣን ትእዛዝ መሰረት መሆኑ በቅድመ ሁኔታነት እንዳይቀመጥ በሕጉ ተደንግጓል።

**የቤተሰብ አባል ለመባል ብቁ የሆነው ማነው?**
የቤተሰብ አባል ማለት ልጅ፣ ወላጅ፣ የትዳር ጓደኛ፣ የተመዘገበ የኑሮ አጋር፣ አያት፣ የልጅ ልጅ ወይም እህት ወይም ወንድም ነው።

**አንድ አሰሪ አንድ ሰራተኛ PSST ለምን እንደሚጠቀም ዝርዝር መረጃ መጠየቅ ይችላል?**
አይችሉም። ሰራተኞች PSST የሚጠቀሙበትን ምክንያት የማጋራት ግዴታ የለባቸውም። አሰሪዎች ለ PSST ከተፈቀደው ሶስት ተከታታይ የስራ ቀናት በላይ ሰራተኛው ከስራ ከቀረ ምክንያቱን የሚያስረዳ የሰነድ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊጠይቁ ይችላሉ። አሰሪዎች ለምን አገልግሎት እንደተጠቀመ መጠየቅ አይችሉም። ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎ የእኛን <u>አጠቃላይ ጥያቄና መልስ</u> ይመልከቱ።

**አሰሪ ሰራተኛው PSST የተጠቀመበትን ምክንያት ማስረጃ እንዲያቀርብ መጠየቅ የሚችለው መቼ ነው?**
አንድ ሰራተኛ ለሶስት ቀናት ያህል ከስራ ከቀረ በኋላ፣ አሰሪው PSST በቀጣይነት መጠቀምን አስፈላጊ መሆኑን የሚያስረዳ ሰነድ እንዲቀርብለት መጠየቅ ይችላል። ሰራተኛው ለምን አገልግሎት እንደተጠቀመበት ሳያስረዳ፣ አገልግሎቱ ግን የተፈቀደ መሆኑን መግለጽ ይበቃዋል። <u>አሰሪዎች የማረጋገጫ ሰነድ የግድ መጠየቅ የማያስፈልጋቸው</u> ሲሆን፣ አሰሪዎች በዚህ ወቅት በተቻለ መጠን እንደሁኔታው ተቀያያሪ እንዲሆኑ እናበረታታለን።

ስለ ማረጋገጫ እና ለማረጋገጫ የሚከፈል ክፍያ ጋር የተያያዙ ደንቦችን በተመለከተ ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የእኛን <u>አጠቃላይ ጥያቄ እና መልስ</u> ይመልከቱ።

**አንድ ሰራተኛ PSST እንዲጠቀም ማስገደድ ይችላሉ?**
አይችሉም። አሰሪዎች በሕጉ በሌላ መልኩ ለሚሸፈን ከስራ መቅረት ሰራተኞች PSST እንዲጠቀሙ ማስገደድ አይችሉም።

**አሰሪው የታመመ ሰራተኛ ወደ ቤት እንዲሄድ ማስገደድ ይችላል?**
የ PSST ሕግ አሰሪው የታመመ ሰራተኛውን ወደ ቤት ከመላክ አይከለክለውም። አንድን ሰራተኛ ወደ ቤት መላክ ሕጋዊ መሆን አለመሆኑን የሚወስኑት ለሌሎች የግዛት እና የአካባቢ ሕጎች ናቸው። ለምሳሌ፣ የ Department of Health (የጤና ክፍል) ደንቦች አንድ የምግብ አገልግሎት ሰራተኛ እንደ ትውከት ያሉ ምልክቶች ወይም ትኩሳት ያለበት የቆሰለ ጉሮሮ ያለበትን ሰራተኛ አሰሪው ወደ ቤቱ መላክ እንዳለበት ይደነግጋሉ። ለተጨማሪ መረጃ፣ <u>Washington Administrative Code 246-215</u> ይመልከቱ ወይም ለ <u>Seattle-King County Public Health Department</u> ያሳውቁ።

**አንድ ሰራተኛ ወረርሽኝ ወደተቀሰቀሰበት ሃገር ደርሶ በመምጣቱ ምክንያት አሰሪው እንዳይሰራ ሊከለክለው ይችላል?**
ወደ አንድ የተወሰነ ሃገር ወይም ክልል ጉዞ ማድረግ አንድ ሰው ለ COVID-19 ስለመጋለጡ አስተማማኝ ጠቋሚ አይደለም። ለ COVID-19 ወረርሽኝ መቀስቀስ ወይም መንስኤነት አንድ የተወሰነ ቡድን በተለይ ዒላማ መደረግ የለበትም። አድሎንና የተዛባ መረጃ ስርጭትን እንዴት መከላከልና ምላሽ መስጠት እንደሚቻል መረጃ ለማግኘት <u>እዚህ ላይ ጠቅ ያድርጉ</u>። በአንድ ሰራተኛ የብሔር ማንነት ወይም የመጣበት ቦታ ላይ ተመስርቶ አሉታዊ የሆነ የስራ ቅጥር እርምጃ መውሰድ አድሎ ወይም ልዩነት በማድረግ ሊያስጠይቅ ይችላል። ለተጨማሪ መረጃ፣ <u>Office of Civil Rights (የሲቪል መብቶች ጽ/ቤት)</u> በስልክ ቁጥር 206-684-4500 ያነጋግሩ።

**አንድ ሰራተኛ የተጠራቀመ PSST ከተጠቀመ ወይም የተጠራቀመ ፈቃድ የሌለው አዲስ ሰራተኛ ከሆነስ?**

Seattle Office of Labor Standards

አንድ አሰሪ ሰራተኛው እንዲጠቀም የሚፈቅድለት የተጠራቀመ የ PSST ሰዓቱን ብቻ ነው። አሰሪዎች በራሳቸው ውሳኔ መሰረት ተጨማሪ ፈቃድ ከክፍያ ጋር ሊሰጡ ወይም የሽርሽር ጊዜ ወይም የተጠራቀመ ፈቃዳቸውን እንዲጠቀሙ ሊፈቅዱ ይችላሉ። ሌሎች ሕጎችም አሰሪው ለሰራተኞቹ ፈቃድ እንዲሰጥ ይጠይቃሉ፤ እነርሱም፡- Family and Medical Leave Act (የቤተሰብ እና የሕክምና ፈቃድ አዋጅ)፣ Washington State Paid Family Medical Leave (የዋሺንግተን ግዛት በክፍያ የቤተሰብ የሕክምና ፈቃድ)፣ እና የፌዴራል፣ የግዛትና የአካባቢ የአካል ጉዳተኞች ሕጎች ናቸው።

ማርች 18/2020 የዩናይትድ ስቴትስ መንግስት የድንገተኛ ጊዜ ሕግ ያወጣ ሲሆን፣ በዚህ ሕግ መሰረትም አንዳንድ ሰራተኞች የተጠራቀመ PSST ባይኖራቸውምን እንኳን ከ COVID-19 ጋር በተያያዙ ምክንያቶች የሕመም ፈቃድ እንዲወስዱ ይፈቀድላቸዋል። ይህ ሕግ ኤፕሪል 2/2020 አካባቢ ተግባራዊ መሆን ይጀምራል። አዲስ መረጃ በተገኘ ቁጥር OLS ይህን ጥያቄና መልስ ያዘምናል።

**አንድ ሰራተኛ ያልተጠቀመበትን PSST ወደ ክፍያ ያለው ፈቃድ ልገሳ ዕቅድ በመለገስ PSST የሚያስፈልጋቸውን የስራ ባልደረቦቹን ማገዝ ይችላል?**
አዎ፣ አሰሪው ይህን የሚፈቅድ ፕሮግራም ካለው። (ሕጉ ይህን እንዲያደርግ አያስገድድም።)

**አንድ ሰራተኛ PSST ለመውሰድ የሚያስፈልገውን ሰዓት የሚሸፍንለት ሌላ ሰው መፈለግ አለበት?**
የለበትም። አሰሪው ሰራተኛው የ PSST ሰዓቱን የሚሸፍንለት ሌላ ሰው እንዲፈልግ ማስገደድ አይችልም።

**ሰራተኛው paid sick እና safe time ከመጠቀም ይልቅ ፈረቃዎችን መለዋወጥ ይችላል?**
አዎ። አሰሪውና ሰራተኛው ከተስማሙ፣ ሰራተኛው PSST ከመውሰድ ይልቅ ፈረቃዎችን መለዋወጥ ይችላል።

**የ Seattle Public Schools (SPS፣ የሲያትል የሕዝብ ት/ቤቶች) ሰራተኞች በ Seattle Paid Sick እና Safe Time ሕግ ይሸፈናሉ?**
አይሸፈኑም። ነገር ግን፣ አንዳንድ የ SPS ሰራተኞች በ Washington ግዛት Paid Sick Leave ሕግ ሊሸፈኑ ይችላሉ። ስለ ግዛት ጥበቃዎች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት፣ ይህን ይጎብኙ፡- https://lni.wa.gov/workers-rights/leave/paid-sick-leave/።

**አንድ ሰራተኛ በሕግ ጥበቃ ከተሰጣቸው ምክንተቶች ውጭ ላሉ ምክንያቶች PSST መጠቀም ይችላል?**
አዎ። አሰሪው በሕጉ ላልተሸፈኑ ጉዳዮች PSST መጠቀምን ሊፈቅድ ይችላል።

**በዚህ ሕግ ስር የተሰጡ መብቶች ወይም ግዴታዎችን በተመለከተ ተጨማሪ ጥያቄዎች ቢኖሩኝ ማንን ደውዬ ማናገር እችላለሁ?**
እባክዎ ለ Seattle Office of Labor Standards (OLS) በስልክ ቁጥር 206-256-5297 ይደውሉ ወይም ቀጣዩን ድረ ገጻችንን ይጎብኙ፡ **http://www.seattle.gov/laborstandards**። ጥያቄዎችዎን ልንመልስና የመረጃ ግብዓቶችን ልናቀርብ እንችላለን!

**ስለ COVID-19 (ከዚህ በፊት ኖቭል ኮሮናቫይረስ የሚባለው) እና ለመዘጋጀት መውሰድ ስለምችላቸው እርምጃዎች ተጨማሪ መረጃ ማግኘት የምችለው የት ነው?**
ለተጨማሪ መረጃ፣ የ Public Health – Seattle & King County ድረ ገጽን በመጎብኘት ስለ COVID-19 የተዘጋጀውን ሰፊ ጥያቄና መልስ ማየት ይችላሉ፤ ይህም ለአጠቃላዩ ሕዝብ፣ ለትምህርት ቤቶች፣ ለስራ ቦታዎችና ለጤና እንክብካቤ ሰራተኞች ዝግጁነት የሚሆኑ ምክረ ሃሳቦችን በስፋት የያዘ ነው።

**አዲስ ነገር!**ይህን ድረ ገጽ በመጎብኘት **Covid-19 ተጽእኖ ሳሳደረባቸው ማህበረሰቦች የሚሆኑ የመረጃ ምንጮችን ይመልከቱ**።

በዚህ ሰነድ ውስጥ የቀረበው መረጃ ሕጋዊ ምክር ባለመሆኑ ሕጎችና ደንቦችን በመተካት አገልግሎት መስጠት የለበትም።
የተሻሻለበት ቀን፡- 4/8/2020